# ሠቅያኔ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

Amara Survival For Ethiopia's Unity Organization (ASEUO)



የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ልዩ | ዕትም፳፮ | ቀን: ነሓሴ ፳፯ | በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ


## የብአዴን አበረታች ጅምሮች!!

ኢትዮጵያ ሀገራችን የተጋፈጠችውን የ27 ዓመታት የግፍና የዘረኛ አገዛዝ ከጫንቃዋ ላይ አሽቀንጥራ ለመጣል በለውጥ ማዕበል ውስጥ ትገኛለች። ለውጡ መልካም ዕድሎችን እንደፈጠረ ሁሉ፣ ተግዳሮቶችንም መደቀኑ አሌ አይባልም። ይህ ለውጥ፣ ከሁሉም በላይ፣ የዐማራውን ስቃይና ስደት የሚገታ እንደሚሆን ይታመናል።

ባለፉት 27 ዓመታት ውስጥ፣ ከዚያም ቀደም ብሎ፣ የወያኔዎች ዘረኛ አገዛዝ ሙሉ ኃይሉን አስተባብሮ የዘመተው ጠላቴ ነው ባለው የዐማራ ሕዝብ ላይ መሆኑ ፀሐይ የሞቀው፣ ዓለም ያወቀው እንደሆነ ግልጽ ነው። በወያኔዎችና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው የተባበረ ደባ፣ ዐማራው ከሰማይ በታች ሊደርስ የሚችል በደልና ሥቃይ ሁሉ የተፈጸመበት ሕዝብ መሆኑን፣ እንኳን ዐማራው፣ ወንጀለኞቹ እራሳቸውም የማይክዱት ጉዳይ ነው። ይህንን ታሪክ ይቅር የማይለውን በደል የፈጸሙት ከመጠየቅ ይልቅ፣ በሹመት ላይ ሹመት እየተደረበላቸው አሁንም በበደሉት ሕዝብ መሃል በይቅርታ ጠያቂነት ኑሩ ቢባሉ፣ ማን ደፍሮን በሚል ትዕቢት፣ እያንገራገሩ መሆኑ እየታዬ ነው። የለውጥ ሐዋሪያ የሆነው ቡድን የማይሸፈነውን ወንጀላቸውን በመሸፈን ከለውጡ ጋር ቁሙ ቢላቸው፣ ሤራ ላይ በመጠመድ በየአካባቢው በሚያደርጓቸው የጥፋት ሥራዎች ተጠምደው ይታያሉ። ያም ሆኖ፣ ሕጋዊ እልባት ያላገኘው እና ዳኝነት የራቀበት፣ ፍትሕና ርትዕ የተነፈገው የዐማራ ደም ጩኸቱን ቀጥሏል።

በዐማራው ላይ የተፈጸመው ግፍ፣ መፈናቀልና ግድያ እየከፉ መምጣትና ባራቱም ማዕዘን የጩኸቱ መበራከት፣ ዐማራ ነን ብለው የሚያምኑ ወገኖች ዐይናቸውን እንዲገልጡ በማስቻሉ፣ ዐማራው እራሱን ቀና አድርጎ የእጣ ፋንታው ወሳኝ እሱ ብቻ መሆኑን ማሳየት ከጀመረ ውሎ አድሯል። በቅርብ ጥቂት ወራት ውስጥ፣ በወያኔዎች የተተበተበ ኋላ ቀር ፖለቲካ ውሉ እንደጠፋበት ልቃቂት ሲጎለጎል፣ ወንጀለኞችና ዘረኞች እርቃናቸውን መቅረት ሲጀምር፣ የዐማራው የወደፊት እንደ ሕዝብ የመኖርና መብቱን የማስከበር መልካም ሁኔታዎች እየተፈጠሩ መምጣታቸው እሙን ነው። ለዚህ ደግሞ ለዘመናት በወያኔ አመራር እግር ተወርች ተይዞ የነበረው በስም ብቻ፣ የዐማራ ወኪል የነበረው የብአዴን ፖለቲካዊ ትንሣዔና ከዐማራው ሕዝብ ጋር ለመቆም ያሳየው እምቢተኛነትና እየወሰደ ያለው ሥልታዊ እርምጃ እጅግ የሚያበረታታ ብቻ ሳይሆን፣ የተስፋ ስንቅም ሆኗል።

የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ በተለይ በቅርብ የወሰዳቸው ባለ12 ነጥብ ቁልፍ ውሳኔዎች የቆመለትን የዐማራ ሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ለማሳካት የቆረጠና ሮሮና ችግሩን ማዳመጡን ያሳየ ነው ለማለት ያስደፍራል። ጅምሩ መልካምና ይበል የሚባል ስለሆነ፣ የዐማራ ኅልውና ለኢትጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ይበል! ግፋ! እኛም ከጎንህ ነን ለማለት ይወዳል። ይህ አካሄድ ለመተባበርና በጋራ ለመሥራትም ፈር ቀዳጅ እንደሆነ ድርጅታችን ያምናል።

በዚሁ የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ባወጣው ባለ12 ነጥቦች መግለጫው መግቢያ ላይ «የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ማእከላዊ ኮሚቴ ነሐሴ 17 እና 18 ቀን 2010 ዓ.ም ለሁለት ቀናት ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ በብአዴን 12ኛ መደበኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ረቂቅ ሪፖርትና ለጉበዔው በሚቀርቡ ሌሎች ወቅታዊና መደበኛ ጉዳዮች ላይ ተወያቶ የተለያዩ ውሳኔዎችን አሳልፏል፡፡» ይላል።

ከእነዚህ ባለ12 ነጥብ  የአቋም መግለጫዎች ውስጥ በርካቶቹ ዐኅኢአድ የዐማራውን ማንነትና ጥቅም ለማስከበር እንደማታገያ መርሕ ይዟቸው የነበሩ ቁልፍ አቅጣጫዎች በመሆናቸው፣ የዐማራውን ኅልውና አስጠብቆ የኢትዮጵያን አንድነት ለማረጋገጥ ለተያያዝነው ትግል እና ለዚህ ዓላማ ከቆሙ ኃይሎች ጋር ለመተባበር  ጥርጊያ መንገድ ከፋች እንደሆኑ ዐኅኢአድ ይገነዘባል። ዐኅኢአድንና ብአዴንን በትልግ አቅጣቻቸው በትይዩ ከሚያስቆሙና ከሚያጎራብቱ አውራ መርሆዎች ውስጥ፡-

- የዐማራ ሕዝብ በማንነቱ ሳይገለል ከቦታ ቦታ ተዘዋውሮ የመኖር፣ የመሥራትና ንብረት የማፍራት መብቱ የሚከበርበት፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ የክልሎች አከላል እንደገና የሚታይበትንና የሚሻሻልበትን መንገድ፣
- ስለሕገ መንግሥቱ መሻሻል አስፈላጊነትና የመለወጡን አግባብነት ያመላከተው የውሳኔ ነጥብ፣
- የግለሰብ ነፃነት የሚጠበቅበትና የቡድን ነፃነትና መብት መጣጣም አስፈላጊነት የነቀሰው ነጥብ፣
- በሱዳንና በኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ ያለውን ችግር በተመለከተ ብአዴን የያዘው ፍንትው ያለ አቋም ተጠቃሾች ሲሆኑ፣ እነዚህ ብአዴን ያወጣቸው አንኳር አዳዲስ አቅጣጫዎች ያፈጻጸምና የትግበራ አካሄዳቸው ዝርዝር ወደፊት ግልጽ እንደሚሆኑ በመገመት፣ ፋይዳቸው ታሪክ ተሻጋሪ የመሆን አቅም እንዳላቸው ዐኅኢአድ ይገነዘባል።
- በሌላ በኩልም፣ የብአዴን የመተዳደሪያ ደንብና ፕሮግራም እንዲሁም የስያሜ ለውጥ ለማድረግ ያለው ውጥን ሀሳብ፣ ከዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ማዕቀፍ ውስጥ መውጣቱንና በትግራይ ነፃአውጭ ድርጅት ከተሰጠው የዳቦ ስም ወጥቶ፣ በዐማራ ማንነቱ ላይ ያነጣጠረ የራሱ መለያና መታወቂያ ባለቤት ለመሆን አቋም መያዙን ያመለከታል።

እነዚህ አንኳር ውሳኔዎች ከዐኅኢአድ መርሕ ጋር ተያያዥና የወል የጋራ ፍላጎትና ዓላማችን በመሆናቸው፣ በነዚህ መሠረትነት ከተቻለ፣ ሁሉንም ዐማራዊ ኃይሎች ባካተተ አንድነት፣ ካልሆነም በትብብር ለሕዝባችን ለመቆምና ኃይልና እውቀታችንና ለማቀናጀት መሠረት ለመጣል የሚያስችል እርምጃ እንደሆነ ዐኅኢአድ ይገነዘባል።

በሌላ በኩልም የመብት ጥሰቶችና የዘር ማጽዳትና ማጥፋት ወንጀሎችን በተመለከተ የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ ለወደፊት ሊወሰዱ የሚገባቸውን ሕጋዊ እርምጃዎችን ያመላከተ ሲሆን፣ ባለፉት 27 ዓመታት በዐማራው ላይ በተፈፀመው  ወንጀልና መፈናቀል ዙሪያ ታሪካዊ እልባት እንዲያገኝም ብአዴን ጠንክሮ መሥራት እንዳለበት ድርጅታችን ያምናል። ምክንያቱም ዘላቂ ሰላምና ተከታታይ ዕድገት ሊገኝ የሚችለው ፍትሕ የተነፈጉ ወገኖች ተገቢ የሆነ ፍትሕ ሲያገኙ ነው።

በዚህ በተከሰተው የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ ብአዴን በተሰመረለት መስመር ሳይወሰንና ከተቀነበበለት ንፍቀ ክበብ በመውጣት፣ የዐማራን ሕዝብ ብሎም ኢትዮጵያን በጠንካራ መሠረት ላይ ለማቆም የያዘው መልካም ጅማሮ አበረታች ነው። እነዚህ ብአዴን የወሰዳቸው አዳዲስ አቅጣጫዎችና አስተሳሰቦች የዐማራውን ችግርና መከራ ከማስወገድ ባለፈ፣ ለዘላቂ ግብ ዋስትና የሚሆኑ ታሪካዊ ዳራ ያላቸው እርምጃዎች እንደሆኑ ዐኅኢአድ ይገነዘባል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የኢትዮጵያ ወሰን አከላለል ተገቢውንና በዓለም ዕውቅና በተሰጣቸው ቋሚ መጠሪያዎችን ሆን ብሎ በመተው የአገሪቱ ወሰን የብሔር/ብሔረሰቦች ክልል እንደሆነ ያስቀመጠው ተገቢ አለመሆኑን ብአዴን ተገንዝቦ፣ ከማናቸውም የጎረቤት አገር ጋር ያለ ወሰን ሲካለል፣ አከላለሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንጂ፣ ከክልል መንግሥታት ጋር እንዳይሆን ጥንቃቄ እንዲደረግ የበኩሉን አቋም እንዲወስድ ለማሳሰብ እንወዳለን። በተለይም ደግሞ ራሱን የትግራይ ነፃ አዉጭ አድርጎ ከሚንቀሳቀስ ከሃዲ ኃይል ጋር በፌዴራል መንግሥት ስም በጓሮ የተደረገን ወይም የሚደረገን ማንኛዉንም ዓይነት ሴራ ዐኅኢአድ መቸዉንም ጊዜ ቢሆን አይቀበልም።

በመጨረሻም ኅብረታችንን የሚያጸና፣ ድርና ማግ የሆነ እውቀትና ብልኅነትን የተላበሰ የተገራ የጋራ አሠራር ልንመሠርት ግድ ከሚለን ሁኔታ ላይ የደረስን መሆኑን፣ ሁላችንም ተገንዝበን፣ ዐማራው በሁለንተናዊ ዐቅሙ የጎለበተ እንዲሆን በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ የየበኩላችን አስተዋጽዖ ለማድረግ ዝግጁ መሆን ይጠበቅብናል። በመልካም ባህላችን እና ዐማራዊ እሴቶቻችን ላይ ተመሥርተን፣ ባለፉት ዘመናት ትውልዱን ፊትና ጀርባ ያደረጉ ጉዳዮችን ወደኋላ ትተንና ቀሪዉንም ለሕግ ክፍት አድርገን፣ ወደፊት ሊያራምዱን በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረታችን አድርገን፣ ለተሻለ ውጤት ለመብቃት ብሔራዊ እርቅና መግባባት የሚወርድበት መንገድ ማመላከት ከሁሉም ሀገሬንና ወገኔን እወዳለሁ ከሚሉ ወገኖች የሚጠበቅ ነው። ያለፉ ተቃርኖዎችን በሰለጠነ መንገድ የሚፈታበትንና የሰከነ የጋራ የፖለቲካ ልንመራ የሚያስችለንን ምኅዳር መፍጠር እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህ ከሆነ የማንዘለው ከፍታ፤ የማናልፈው መሰናክል አይኖርም።

ለዚህ ሁሉም የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ የውሳኔ ሀሳብ በመጪው ጉባኤ ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ተግባር የሚለወጥበትን ፍኖተ ካርታ ይፋ እንደሚሆን እምነታችን የጸና ነው። ይህ ሲሆን ዐማራው ያለፈውን መልካም ታሪኩንና ዝናውን አድሶ፣ ለመጭው ዘመን የከፍታ ጉዞው ታላቅ የኅሊና እና የዝግጁነት ሥንቅ የሰነቀ መሆኑ ማሳያ ይሆናል።

**የዐማራ ኅልውና መጠበቅ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!**